የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6[th] Year No. 18
ADDIS ABABA - 28[th] December, 1999

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፺/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ (ማሻሻያ)
አዋጅ ........................................... ገጽ ፩ሺ፪፻፴፬

CONTENTS

Proclamation No. 190/1999
Public Servants' Pension (Amendment)
Proclamation ........................................... Page 1234

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፺/፲፱፻፺፪
## የመንግሥት ሠራተኞችን የጡረታ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የመንግሥት ሠራተኞችን የጡረታ አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩፻፺/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፪፻፱/፲፱፻፶፭ /እንደተሻሻለ/ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል ፤

፩· የአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተተክቷል ፤

"፫· "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ቋሚ ሠራተኛ ሲሆን ፤

ሀ) ቢያንስ ሃምሣ በመቶ የመንግሥት ባለቤትነት ባለበት ድርጅት ቋሚ ሠራተኛ የሆነን፤

ለ) በማናቸውም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ውስጥ በሹመት ተመድቦ የሚሠራን ፤

## PROCLAMATION NO. 190/1999
## A PROCLAMATION TO AMEND THE PUBLIC SERVANTS' PENSION PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Public Servants' Pension Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Public Servants' Pension (Amendment) Proclamation No. 190/1999."

2. *Amendment*

The Public Servants' Pension Proclamation No. 209/1963 (as amended) is hereby further amended as follows:

1) Sub Article (3) of Article 4 is deleted and replaced by the following new Sub Article (3):

"3) 'Public Servant' means a permanent employee of a Federal or Regional Government office and includes:

(a) a permanent employee of an organization in which the Government has at least fifty per cent ownership;

(b) a government appointee working in any Federal or Regional Government organ;

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

ሐ) በምርጫ ምክንያት የጡረታ ሽፋን የሚያስገኝ ሥራውን የለቀቀና ሙሉ ጊዜውን በማናቸውም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ውስጥ የሚያገለግል የሕዝብ ተመራጭን ፣ እና

መ) የመከላከያ ወይም የፖሊስ ሠራዊት አባልን፣ ይጨምራል ።"

፪· የአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ተተክቷል ፤

"፬· በዚህ አዋጅ ውስጥ 'የመከላከያ ሠራዊት አባል' የሚለው ሐረግ በመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር ፳፯/፲፱፻፹፰ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል ።"

፫· በአዋጁ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "የጦር ሠራዊት ባልደረባ" የሚለው ሐረግ ተሠርዞ "የመከላከያ ሠራዊት አባል" በሚለው ተተክቷል ።

፬· የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፬ ተተክቷል ፤

"፳፬· ሚስቱ የሞተችበት ሰው የጡረታ አበል

በዚህ አዋጅ ባሏ ለሞተባት ሴት የተደነገገው ሚስቱ ለሞተችበትም ሰው በተመሣሣይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል ።"

፫· የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፪/፩/ የተደረገው ማሻሻያ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምሥረታ ጀምሮ ይህ አዋጅ እስከጸናበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ላገለገሉ የሕዝብ ተመራጮችም ተፈጻሚ ይሆናል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

(c) a representative who had resigned from his pensionable job because of election and serves in any Federal or Regional government organ on full time basis;

(d) a member of the Defence or Police force working in any Federal or Regional Government organ."

2) Sub Article (4) of Article 4 is deleted and replaced by the following new Sub Article (4):

"4) In this Proclamation, the phrase "Member of the Defence Forces" shall have the meaning given to it in the Defence Forces Proclamation No. 27/1996."

3) The phrase "Member of the Armed Forces" is deleted wherever it appears in the Proclamation and replaced by the phrase "Member of the Defence Forces."

4) Article 24 is deleted and replaced by the following new Article 24:

"*24. Widower's Pension*

The Provision of this Proclamation provided for a widow shall equally apply to widower's pension."

3. *Transitory Provisions*

The amendment under Article 2(1) of this Proclamation shall also be applicable to representatives of the people who had served within the period starting from the establishment of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and until the effective date of this Proclamation.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 28th day of December, 1999.

Done at Addis Ababa, this 28th day of December, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE